# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

# Commercial Bank of Ethiopia

## ጋዜጣዊ መግለጫ

## የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሐብት ማሰባሰብ የህዝብ ድጋፍን አጠናክሮ የማስቀጠል እንቅስቃሴን በተመለከተ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## ነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም.

እንደሚታወቀው የአንድነታችን ህብረ-ዜማ የለውጣችን የድል አርማ የሆነው ታላቁ ህዳሴ ግድባችን በዩኒት ዘጠን ሁለተኛው ተርባይን የሃይል ማመንጨት ስራ መጀመሩን በክቡር ሚንስትራችን ዶክተር አብይ አህመድ ነሃሴ 04 እና 05/2014 ዓ.ም የተበሰረ በመሆኑና የሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌትም በስኬት በመጠናቀቁ እንኳን ደስ አለን!! እንኳን ደስ አላችሁ!!!

ስለሆነም በዚህ አጋጣሚ ይህ በመንግስታችንና በህዝባችን የጋራ እርብርብ እየተገነባ ያለው በአፍሪካ ግዙፉ የኃይል ማመንጫ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክታችን እንደተለመደው የልማት አርበኛ በሆነው ህዝባችን ድጋፍ፤ በመንግስት አቅጣጫ፤በሁሉም ድርጅቶች/ተቋሞችና ባንኮች ተሳትፎ፤በመንግስት ልማት ድርጅቶች አጋርነት እና በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የልማታዊ አጋርነትና ተሳትፎ ብሎም የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባበሪነትና ክትትል፤በአጠቃላይ በመላው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሞራል፣በእውቀትና በጉልበት ድጋፍ ግንጋታው ወሳኝ ምእራፍ ላይ መድረሱ ለዚህ ታላቁ የህዳሴ ግድባችን/GERD ስኬት ላበረከቱ ሁሉ የከበረ ምስጋና ይገባል፡፡

- በተለይ ደግሞ ከምንም በላይ ገንዘባቸውን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መቆጠብን የመረጡትን እጅግ በጣም ከልብ እያመሰገንን ባንኩ ተግባራዊ ባደረጋቸው የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል የሚያነቃቁ ስልታዊ አሰራሮች አማካኝነት በርካታ ሃብት በማሰባሰብ ይህንኑ ሃብትንም መልሶ ለሃገራችን ልማትና ወሳኝ ለሆኑ ፕሮጀክቶች ማዋሉ እውን ነው፡፡ በመሆኑም እ.ኤ.አ እስከ ሃምሌ 31 ቀን 2022 ድረስ ባንኩ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል የተለያዩ ግንባታዎች እና አገልግሎቶች አጠቃላይ 425.2 ቢሊዮን ብር ብድር የሰጠ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ /GERD/ ግንባታ እና ለሃይል ማስተላለፊያ ግንባታ ፕሮጀክት ከ149.8

ቢሊዮን ብር በላይ ብድር በማቅረብ የተቀረውን የግድቡን ፍጻሜ እውን እያደረገ ይገኛል።

- ቦንድ የገዙ እና ለታላቁ ህዳሴ ግድብ /GERD/ ገንዘብ በልገሳ የሰጡን ስናይ ደግሞ እ.ኤ.አ እስከ 30 ሰኔ 2022 ድረስ ባንካችን የተደረገው በብር እና በውጭ አገር ገንዘብ ለህዳሴው ግድብ የተደረገው ማሰባሰብ እጅግ በጣም ትልቅ ነው። ይኸውም
    - በባንካችን ባሉ 1,832 ቅርንጫፎች በኩል ከቦንድ ሽያጭ የተሰበሰበ **ብር 8,629,934,587.80** (**ከ8.6 ቢሊዮን ብር በላይ**) ሲሆን በልገሳ የተገኘ **ብር 208,767,731.19** (**208 ሚሊዮን ብር በላይ**) ነው፡፡
    - እንዲሁም ከውጭ አገር ቦንድ ሽያጭ በውጭ ምንዛሬ **36,956,245 USD** (37 ሚሊዮን ዶላር) ፣ **3,270,220 EUR** (3.3 ሚሊዮን ዩሮ) እና **1,1085,300 GBP** (1.1 ሚሊዮን ፓውንድ) ገቢ አደርጓል፣
    - በቅርቡም ባንካችን ጊዜው ደርሶ ከሚታደሰው ቦንድ ውጭ በተጨማሪ ከ **200,000,000** (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) በላይ በስሙ ቦንድ ገዝቷል።
    - የባንኩ ሠራተኞች ደግሞ ብር **19,754,750** (**ከ19 ሚሊዮን ብር በላይ**) ቦንድ በመግዛት ግንባታው እንዲፋጠን ስላደረጉት ሀገራዊ ተሳትፎ ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው፡፡
- በሌላ በኩል ደግሞ ለግድቡ እዚህ ለማድረስ አስቸጋሪውን የአየር ሁኔታ በመቋቋም በታላቁ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት/GERD/ ጠንካራ ስራ ውስጥ የተሰማሩ ሰራተኞች እንደዚሁ እጅጉን ሊመሰገኑ ይገባልና በባንኩ ስም እናመሰግናለን፡፡
- ከውድቀት እየታደገ ያለው አመራር በሁሉም ውጣ ውረዶች ውስጥ እየታገለና ከባዱን ሚና እየተጫወተ ያለ በመሆኑ የሚመሰገንና የሚደነቅ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዋና ሀገራዊ ልማት መርሃ ግብሮች ውስጥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሚና በተለይም በኃይል እና በታላቁ ህዳሴ ግድብ /GERD/ ፕሮጀክት ስራ ውስጥ ያለውን ሚና እንደሚከተለው ይገለፃል።

i. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስተዋፅኦ ተወዳዳሪ የሌለውና በጣም ከባድ ፋይናንስ ማቅረብ ፣ ለፕሮጀክቱ ግብዓት ማስመጣት ፣ ለፕሮጀክቱ በቢሊዮን የሚቆጠሩ

አገልግሎቶችን ማረጋገጥ ፣ ለፕሮጀክቱ ክፍያዎችን ማመቻቸት እና በፈንድ ማሰባሰብ ላይ ድጋፍ ወዘተ.

ii. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተጠራቀመ ገንዘብ ለጋራ ጉዳይ ጥቅም ላይ ስለሚውል ከቁጠባ ዋና ዓላማ የበለጠ ሁሉንም ዜጎች ይረዳል። በተጨማሪም፡-

- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵየውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለግድቡ የሚያደርጉትን የገንዘብ ስጦታ ይበልጥ ለማጠናከር ከዚህ ቀደም ከሚጠቀምባቸው መንገዶች በተጨማሪ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሰፊው በመጣመርና ቅስቀሳ በማድረግ የሃብት አሰባሰቡን የማስቀጠል ስራ መስራት፤
- ባንካችን ከመደበኛው የባንክ አሰራር በተጨማሪ የሃብት ማሰባሰብ መተግበሪያ (በ Android, iphone እና website) ከኢትየጵያ ንግድ ባንክ ድረ ገፅ ላይ በቀላሉ ማግኘት ማውረድ የሚቻል መተግበሪያ በመጠቀም በተለይ በውጭ ከሚኖሩ ትውልደ ኢትዮያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በቀላሉ በልግሳ መልክ ለግድቡ ሃብት እንዲሰባሰብ ማስቻል፤
- ኢትዮጵያውያን፣ በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ወዳጆችዋ ለህዳሴው ግድብ እውን መሆን ቦንድ በመግዛትና በልገሳ ፋይናንስ በማድረግ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ መደገፍና ማበረታታት፤

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለህዳሴው ግድብ በሁሉም አስፈላጊ ድጋፎች ሁሉ ከጎን በመገኘት ፕሮጀክቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያለውን ጠንካራ ቁርጠኝነት እንደሚያሳይ መግለፅ ይወዳል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአጠቃላይ የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነት መወጣት እንዲችል እና በተለይም የህዳሴ ግድባችን እንዲጠናቀቅ ባለድርሻ አካላት በሙሉ እንዲሰሩ እና ታላቁን ህዳሴ ግድብን በትኛውም መንገድ እንዲደግፉ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

**አቤ ሳኖ**
**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት**
**ነሀሴ 23 ቀን 2013 ዓ.ም**

---